Fact Sheet

## ስለእኛ

የትምህርት ሚኒስቴር በአስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሠረት በአጠቃላይና ከፍተኛ ትምህርት ዘርፎች የተዋቀረ ተቋም ሲሆን በአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ ከ49ሺ በላይ የሚሆኑ የቅድመ አንደኛ፣ የአንደኛ ደረጃ፣ የመካከለኛና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ 47 ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን፣ የትምህርትና ሥልጠና ባለስልጣን እና የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎትን የያዘ ነው፡፡

ተግባርና ኃላፊነቶቹም የአጠቃላይና የከፍተኛ ትምህርት፣ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎች፣ ህጎችና እና ፕሮግራሞች መቅረጽ፣ የሥርዓተ-ትምህርት ማዕቀፍ ማዘጋጀት፣ የትምህርት እና የትምህርት ተቋማትን ስታንዳርድ ማውጣት፣ ሀገራዊ የብቃት ማዕቀፍ ማዘጋጀትና በሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ፣ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲውን መሠረት መተግበር፣ ሀገር አቀፍ ፈተናዎች ማዘጋጀትና ጥራትን ማረጋገጥ፣ የፈፃሚን አቅም መገንባትና ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣ ወዘተ. ያካትታል፡፡

## ስለፖርታሉ

በትምህርት ሚኒስቴር የተዘጋጀው ዌብ-ፖርታል ለአጠቃቀም ቀላልና  ምቹ እንዲሁም በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ 49 ሺህ የሚጠጉ ት/ቤቶችን መረጃዎች በአግባቡ ሰንዶ የያዘ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ሲሆን ለጋሾች፣የቀድሞ ተማሪዎች፣ ባለሀብቶች፣ የአካባቢው ማህበረሰብ አካላት ወ.ዘ.ተ. ለማገዝ የሚፈልጉት አካባቢና ት/ቤት ምን ይጎድለዋል የሚለውን ጥያቄ በቀላሉ የሚመልስ ነው፡፡

ይህ ፖርታል በሀገሪችን ያሉ ትምህርት ቤቶችን አጠቃላይ መረጃ የያዘ ከመሆኑም በተጨማሪ በየጊዜው የሚደረጉ የት/ቤቶች መሻሻሎችን የሚያሳይም ነው ፡፡

Web-portal: sip.moe.gov.et

CamScanner

## የሕዝብ ንቅናቄው ዋና ዓላማ

- የትምህርት ጥራት ችግሮች መንስኤዎች ዘርፈ ብዙ ቢሆኑም፤ ትምህርት ቤቶች ለመማር ማስተማር ምቹ አለመሆናቸው ከመሰረታዊ ችግሮች አንዱና ዋነኛው ነው። በሀገራችን 49ሺ ከሚሆኑ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከ86% በላይ የአንደኛና የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች እንዲሁም ከ71% በላይ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ከስታንደርድ በታች ናቸው፡፡ ይህም ትምህርት ቤቶቹ ለመማር ማስተማር አስፈላጊና የተሟሉ መሠረተ-ልማቶች ስለሌላቸው ተማሪዎች በተጓደለ የትምህርት ከባቢ ውስጥ እንዲማሩ ተገደዋል። በመሆኑም በየደረጃው ያሉ ተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን እውቀት፣ ክህሎትና የባህሪ ለውጥ ማምጣት አለማቻላቸው በግልጽ ታይቷል፡፡
- ይህን ችግር በመንግሥት አቅም ብቻ ለመፍታት ቢታሰብ ከሶስት አስርት አመታት ያላነሰ ጊዜ ሊወስድ ይችላል። ስለዚህ ይህን ሰፊ ችግር መፍታት የሚቻለው ሥርዓት አበጅቶ በዘላቂነት የማህበረሰብና የልዩ ልዩ የትምህርት ባለድርሻ አካላት ማለትም በየደረጃው ያሉ አመራሮች፣ የአካባቢው ማህበረሰብ፣ የቀድሞ ተማሪዎች፣ ታወቂ ግለሰቦች፣ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን፣ ባለሀብቶች፣ ወዘተ. በትውልድ ቦታቸው፣ በተማሩበት ቦታ፣ በሚሰሩባቸውና በሚኖሩባቸው አካባቢ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች መሰረተ-ልማቶችን ማሻሳል ሲቻል ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህን ትምህርት ቤቶች በሕዝብ ንቅናቄ አግባብ ለማሻሻል እቅድ ተዘጋጅቷል፡፡ የዚህ የሕዝብ ንቅናቄው ዋና ዓላማ በየደረጃው ያሉ ማህበረሰብና ልዩ ልዩ አካላትን በማሳተፍ የትምህርት ቤቶችን መሠረተ-ልማት ለማሻሻል እንዲሁም በዘላቂነት የመማር ማስተማሩን ሂደቱን በባለቤትነት እንዲደግፍ ለማስቻል ነው፡፡

## በሀገራዊ ንቅናቄው የሚጠበቁ ውጤቶች

- የሕዝብ ንቅናቄ አደረጃጀት በመፍጠር ወደ ተጨባጭ ሥራ መግባት፤ ትምህርት ቤቶችን ማሻሻል፡፡
- የትምህርት ቤቶችን ነባራ ሁኔታ መለየት፤ እንዲሻሻሉ ማድረግ፡፡
- በየደረጃው ባለው ማህበረሰብና ልዩ ልዩ አካላት ተሳትፎ የትምህርት ቤቶችን መሠረተ-ልማት ለማሻሻል የየራሳቸውን ድርሻ በሃላፊነት መወጣት፡፡
- የትምህርት ቤት መሠረተ-ልማት ለማሻሻል የአሠራር ሥርአት በመዘርጋት በዘላቂነት እንዲቀጥል ማደረግ፡፡

CamScanner

- ማህበረሰቡና ልዩ ልዩ አካላት በሙያቸው፣ በእውቀታቸውና በጉልበታቸው እስተዋጽኦ ማድረግ፡፡
- በማህበረሰቡና በልዩ ልዩ አካላት ተሣትፎ የትምህርት ቤቶች መሠረተ–ልማቶች ማሻሻል፡፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

CamScanner